## የካንሰር ማጣሪያ ምርመራ ምንድነው?

የካንሰር ማጣሪያ ምርመራዎች የካንሰር ምልክቶችን አስቀድሞ ለመመልከት ይረዳሉ። ምርመራዎቹ በሴሎች ላይ ለውጦችን ሊያገኙ ወይም በሰውነትዎ ውስጥ ወደፊት ካንሰር ሊያስከትሉ የሚችሉ ኢንፌክሽኖችን ማግኘት ይችላሉ።

የአውስትራሊያ መንግስት የአንጀት፣ የጡት እና የማህፀን ጫፍ ካንሰር ምልክቶችን ለማግኘት ሶስት ሀገር አቀፍ የካንሰር ምርመራ ፕሮግራሞችን ይሰጣል። ካንሰር ገና በመጀመርያ ደረጃ ላይ ከተገኘ፣ የመዳን እድሉ ከፍ ያለ ነው።

**አረንጓዴ ወይም ሰማያዊ የሜዲኬር ካርድ ካለዎት የካንሰር ማጣሪያ ምርመራ ፕሮግራሞች ነጻ** ናቸው። የሜዲኬር ካርድ ከሌለዎት ለምርመራዎቹ ምን ያህል እንደሚያስወጣ ከጠቅላላ ሐኪምዎ (GP) ጋር ይነጋገሩ።

## የካንሰር የማጣሪያ ምርመራ ሕይወትዎን ሊያድን ይችላል።

ስለ አንጀት፣ የጡት ወይም የማህፀን ጫፍ ካንሰር የማጣሪያ ምርመራ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እነዚህን ይጎብኙ

- cancersa.org.au
- breastscreen.sa.gov.au
- wellbeingsa.sa.gov.au/cervicalscreening

ተመርምረው ካንሰር ከተገኘብዎት በኋላ ድጋፍ ከፈለጉ፣ **ለካንሰር ካውንስል ደቡብ አውስትራሊያ (SA)** በ **13 11 20** ይደውሉ።



ይህ የመረጃ ምንጭ የተዘጋጀው በ ዌልቢንግ ኤስኤ (Wellbeing SA)፣ ብሬስትስክሪን ኤስኤ (BreastScreen SA) እና ካንሰር ካውንስል ኤስኤ (Cancer Council SA) ነው።

የመረጃ ምንጩ ለመጀመሪያ ጊዜ በ 2017 የተለያየ ቋንቋ እና ባህል ያላቸው ማህበረሰቦች (CALD) የሴቶች የካንሰር ማጣሪያ ምርመራ አምባሳደሮች ፕሮጀክት ወቅት የተሰራ ነው።

Cancer Council SA

ስለ ካንሰር ነፃ* እና ሚስጥራዊ መረጃ እና ድጋፍ ለማግኘት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 9.00 ሰኣት እስከ ምሽቱ 5.00 ሰኣት፡-

- ወደ ካንሰር ካውንስል በ**13 11 20** ይደውሉ
- በኦንላይን በ **cancersa.org.au** ቻት ያድርጉ
- ኢሜይል **askanurse@cancersa.org.au**

ነፃ* የትርጓሜ አገልግሎት በ **131 450** ይገኛል።

*የአካባቢ የስልክ ጥሪ ዋጋ

በዲሴምበር 2022 ተገምግሟል

Amharic | አማርኛ

Cancer Council SA

# የነቀርሳ (ካንሰር) የማጣሪያ ምርመራ

## ካንሰርን አስቀድሞ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል



ካንሰር እንዳለብዎ አስቀድሞ ማወቅ

ለመረጃ እና ድጋፍ

**131120**

**cancersa.org.au**




# የአንጀት ካንሰር የማጣሪያ ምርመራ

## የአንጀት ካንሰር ብዙ ጊዜ ምንም ምልክት ሳያሳይ ያድጋል። የአንጀት ካንሰር ገና በለጋ ደረጃ ላይ ከተገኘ፣ የመዳን እድሉ ከፍ ያለ ነው።

የአንጀት ካንሰር የማጣሪያ ምርመራ የሰገራ ደም ምርመራ (Faecal Occult Blood Test (FOBT)) ማጠናቀቅን ያካትታል። የሰገራ ደም ምርመራ (FOBT) በሰገራዎ ውስጥ የማይታይ ደም ይፈልጋል። ደም ከተገኘ፣ የደሙ መንስኤን ለማግኘት ተጨማሪ ምርመራ ያስፈልግዎት ይሆናል።

በየሁለት አመቱ ብሄራዊ የአንጀት ካንሰር ማጣሪያ ምርመራ ፕሮግራም ከ50-74 አመት ለሆኑ አውስትራሊያውያን ሁሉ ነፃ የሰገራ ደም ምርመራ (FOBT) ጥቅል (ኪት) በፖስታ ይልካል።

**የካንሰር ካውንስል ኤስኤ (SA) የሚከተለውን ይመክርዎታል፡-**

- ዕድሜዎ 50 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በየሁለት ዓመቱ በአንጀት ካንሰር የማጣሪያ ምርመራ ይሳተፉ።
- የሕመም ምልክቶች ካሉብዎ ሐኪምዎን ያነጋግሩ። ምልክቶቹ ከፊንጢጣዎ ደም መፍሰስ፣ ከተጸዳዱ በኋላ በሽንት ቤት ወይም በሽንት ቤት ወረቀት ላይ ደም ማየት፣ ወይም ያልታወቀ የሆድ ድርቀት ወይም ተቅማጥ ያካትታሉ።
- በቤተሰብዎ የአንጀት ካንሰር ታሪክ ካለ የቤተሰብ ሐኪምዎን (GP) ያነጋግሩ።

**እድሜዎ ከ50-74 አመት ከሆነ የሰገራ ደም ምርመራ (FOBT) ጥቅል (ኪት) ከብሔራዊ የአንጀት ካንሰር ማጣሪያ ፕሮግራም በፖስታ ሲመጣ ምርመራውን መፈጸም እና መመለስ አስፈላጊ ነው።**

**ncsr.gov.au**ን ይጎብኙ ወይም ወደ ብሄራዊ የካንሰር ምርመራ መዝገብ በ **1800 627 701** ይደውሉ፡

- የብሔራዊ የአንጀት ካንሰር ማጣሪያ ምርመራ ፕሮግራም ነፃ የሰገራ ደም ምርመራ (FOBT) ጥቅል ( ኪት) መቼ እንደሚልክልዎ ይወቁ
- የሰገራ ደም ምርመራ (FOBT) ጥቅል (ኪት) ከጠፋብዎ ወይም ከተበላሸ ወይም ጊዜው ያለፈበት ከሆነ ምትክ መመርመሪያ ይዘዙ
- ተጨማሪ የመረጃ ምንጮች በቋንቋዎ ያውርዱ።




# የጡት ካንሰር ማጣሪያ ምርመራ

## የጡት ካንሰር ያለ ግልጽ ምልክቶች ሳይኖሩ ሊያድግ ይችላል። የጡት ካንሰር ገና በለጋ ደረጃ ላይ እያለ ከተገኘ፣ የመዳን እድሉ ከፍ ያለ ነው።

የጡት ስክሪን የጡት ኤክስሬይ ነው። መደበኛ የጡት ስክሪን ማድረግ፣ ብዙ ጊዜ ስሜቱ ከመሰማቱ በፊት፣ ገና ትንሽ እያለ እና በቀላሉ ለማከም በሚቻልበት ጊዜ የጡት ካንሰርን ቶሎ ሊያገኝ ይችላል። የጡት ስክሪን በአሁኑ ጊዜ ምልክቶች በሌላቸው ሴቶች ላይ የጡት ካንሰርን ለማግኘት በጣም የተሻለ ምርመራ ነው።

**የካንሰር ካውንስል ኤስኤ እና ብሬስትትካንሰር ኤስኤ (BreastScreen SA) የሚከተለውን ይመክራሉ፡-**

- እድሜዎ ከ50 እስከ 74 ዓመት ከሆነ በየሁለት ዓመቱ የጡት ስክሪን በብሬስትትካንሰር ኤስኤ (BreastScreen SA) ያድርጉ። እድሜዎ ከ40-49 ወይም 75 እና ከዚያ በላይ ከሆነ ነፃ የጡት ስክሪን ሊያደርጉ ይችላሉ።
- ምንም እንኳን እድሜዎ ከ50 ዓመት በታች ቢሆንም ወይም መደበኛ የጡት ስክሪን ቢያደርጉም ለማንኛውም ለውጥ ጡትዎን በየጊዜው ያፈትሹ።
- በጡትዎ ላይ ማንኛውም አይነት ለውጥ ካዩ በተቻለ ፍጥነት ሀኪምዎን ያነጋግሩ። ለውጦች በጡትዎ ላይ እብጠት ወይም የጡትዎ መጠን ወይም ቅርፅ ለውጥ ያካትታሉ።
- በቤተሰብዎ የጡት ካንሰር ታሪክ ካለ የቤተሰብ ሐኪምዎን (GP) ያነጋግሩ።

**ነጻ የጡት ስክሪን ቀጠሮ ለመያዝ ለብሬስትትካንሰር ኤስኤ (BreastScreen SA) በ 13 20 50 ይደውሉ።**

ቀጠሮ በሚይዙበት ጊዜ አስተርጓሚ ከፈለጉ እባክዎን ይንገሯቸው።

**breastscreen.sa.gov.au** ይጎብኙ፡-

- ስለ የጡት ስክሪን ለበለጠ መረጃ ለማግኘት
- በቋንቋዎ የተጻፉ የመረጃ ምንጮች ለማውረድ።



# የማኅጸን ካንሰር የማጣሪያ ምርመራ

## አብዛኛው የማኅጸን ጫፍ ነቀርሳዎችን በመደበኛ የማህፀን ጫፍ ምርመራ መከላከል ይቻላል።

አብዛኛው የማኅጸን ጫፍ ነቀርሳዎችን በመደበኛ የማህፀን በር ምርመራ መከላከል ይቻላል።

1. እራስዎ የሚሰበስቡት ምርመራ፣ ረጅም እጀታ ያለው የጥጥ ናሙና መሰብሰቢያ በመጠቀም የራስዎን ሴሎች ከሴት ብልት መሰብሰብ። ይህንን ምርመራ በሐኪም (GP) ክሊኒክ ውስጥ በግል ሊወስዱት ይችላሉ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ከቤተሰብ ሐኪምዎ (GP) ጋር አስቀድመው ካቀናጁ በቤት ውስጥ ምርመራ ማድረግ ይችላሉ።
2. በቤተሰብ ሐኪም (GP) ወይም ነርስ የተሰበሰበ ናሙና፣ ስፔኩሉም የገባበት እና ህዋሶች ከማህፀን በር ጫፍ የሚሰበሰቡበት ነው።

ሁለቱም አማራጮች እኩል አስተማማኝ እና ውጤታማ ናቸው። የትኛው አማራጭ ለእርስዎ ትክክል እንደሆነ ከጠቅላላ ሐኪምዎ ው(GP) ወይም ነርስ ጋር ይነጋገሩ።

ቀጠሮዎን በሚያስይዙበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- እራስዎ የመሰብሰብ ሂደት በክሊኒኩ መኖሩን ይጠይቁ
- ሊኖሩ ስለሚችሉ ክፍያዎች ይጠይቁ
- ሴት ሐኪም (GP) ወይም ነርስ ይጠይቁ
- ከፈለጉ አስተርጓሚ ይጠይቁ
- ድርብ ቀጠሮ ይጠይቁ።

**የካንሰር ካውንስል ኤስኤ (SA) እና ዌልቢንግ ኤስኤ (Wellbeing SA) የሚከተለውን ይመክራሉ፡-**

- ማንኛውም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ያደረጉ፣ ዕድሜያቸው ከ25-74 የሆኑ እና የማህፀን ጫፍ ያላቸው ሁሉም ሴቶች እና ሰዎች በየአምስት ዓመቱ የማህፀን ጫፍ የማጣሪያ ምርመራ ማድረግ አለባቸው።
- ዕድሜያቸው ከ12-13 የሆኑ ህጻናት ሂውማን ፓፒሎማቫይረስ (HPV) ክትባት ይወስዳሉ። ክትባቱ በነጻ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወይም በሐኪም (GP) ክሊኒክ በብሔራዊ የክትባት መርሃ ግብር ይሰጣል።
- በጾታዊ ግንኙነት ወቅት ያልተለመደ ደም መፍሰስ ወይም ህመም ያሉ ምልክቶች ካጋጠመውዎት ዶክተርዎን ያነጋግሩ።

ለበለጠ መረጃ **wellbeingsa.sa.gov.au/cervicalscreening** ይጎብኙ ወይም የማህፀን ጫፍ ካንሰርን በቶሎ ለማግኘት **cancersa.org.au** ይጎብኙ።